# አልበርት አንስታይን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የኮሌጅ ማመልከቻ ሂደት መመሪያ

**የት/ቤቱ አድራሻ፡**

**School Address:**
11135 Newport Mill Rd.
Kensington, MD 20895
240-740-2700

**Einstein CEEB code:**

**አንስታይን CEEB ኮድ**
210677

| የኮሌጅ ቀነገደብ | ቅጽ ማስረከቢያ ቀነገደብ |
|---|---|
| ኦክቶበር 1 | ኦገስት 29 |
| ኦክቶበር 15 | ሴፕተምበር 17 |
| ኖቬምበር 1 | ኦክቶበር 3 |
| ኖቬምበር 15 | ኦክቶበር 17 |
| ዲሰምበር 1 | ኖቬምበር 3 |
| ዲሰምበር 15 | ኖቬምበር 17 |
| ጃኑዋሪ 1 | ዲሰምበር 4 |
| ጃኑወሪ 15 | ዲሰምበር 18 |
| ፌብሩዋሪ 1 | ጃኑወሪ 5 |

1ኛ

## "Family Connection" አካውንት ፍጠር(ሪ) ናቪያንስ አካውንት/Naviance Account ላይ "ስለራስህ(ሽ) የሚገልፅ የተማሪ መረጃ" ቅጽ ሙላ(ይ)

- Google Waffle አማካይነት "Access Family Connection/ Naviance" ክፈት(ቺ)
- መግቢያ ሎግ - ኢን (Log-in) መረጃ፡- Chrome መክፈቻ የምትጠቀም(ሚ)በት የተጠቃሚ ስም እና ይለፍ ቃል አንድ አይነት ናቸው፣ ወዘተ.
- እዚህ እና AEHS ካውንስሊንግ ገጽ ላይ በቀኝ በኩል የሚገኘውን ስለራስህ(ሽ) የሚገልፅ ቅጽ ሙላ(ይ)።

2ኛ

## "Common Application እና FERPA Waiver" ሙላ(ይ)

- ሁሉም ተማሪዎች "Common Application" አካውንት መክፈት አለባቸው። ተማሪዎች www.commonapp.org ከፍተው ከዚያ በኋላ “Apply Now” የሚለውን መርጠው አካውንት መፍጠር አለባቸው። የማያገናኝ ከሆነ፣ Google Chrome መጠቀም አለብህ(ሽ)
- አካውንቱን ከከፈትክ(ሽ) በኋላ “Common App” የሚለውን ትር ምረጥ(ጪ)። የማመልከቻውን ገፅ ለማግኘት “Education” የሚለውን ከፍተህ(ሽ) ሙላ(ይ)። የአሁኑ ትምህርት ቤትህ(ሽ) አልበርት አንስታይን መሆኑን ከዝርዝሩ ላይ መምረጥህ(ሽ)ን እርግጠኛ ሁን(ኚ)።
- "Education" የሚለው ሰክሽን ከተጠናቀቀ በኋላ “College Search” የሚለውን ትር ክፈት(ቺ)
- ተማሪዎች ምንም እንኳን ለየትኛውም "Common App" ትምህርት ቤት ባይያመለክቱም ከዝርዝሩ ውስጥ ቢያንስ አንድ ትምህርት ቤት መምረጥ አለባቸው
- ከዝርዝሩ ውስጥ ትምህርት ቤቱ ከገባ በኋላ “My Colleges” የሚለውን ትር ምረጥ(ጪ) እና “Recommenders and FERPA” የሚለውን ክፍል ሙላ(ይ)። ይህ ለአልበርት አንስታይን ት/ቤት የአንተ(ቺ)ን ትራንስክሪፕት ወደ ኮሌጆች ለማስተላለፍ እንዲችል ፍቃድ ይሰጣል ማለት ነው።
- እነማን የድጋፍ ደብዳቤ መጻፍ እንዳለባቸው ለመለየት “Assign Recommenders” የሚለውን ክፍል ተጠቀም(ሚ)። አስተማሪዎችህ(ሽ) እና ካውንስለሮች ምላሽ ለመስጠት 20 የትምህርት ቀናት ያስፈልጋቸዋል። ሂደቱ ምን ያህል ጊዜ እንደሚወስድ ለማወቅ በገጹ አናት ላይ ያለውን የጊዜ ሠሌዳ ተመልከት(ቺ)።

3ኛ

## "Common Application and Family Connections" አካውንቱን ክፈት(ቺ)

- Family Connection Account" አካውንት ላይ "ኮሌጆች/Colleges" የሚለውን ትር ምረጥ(ጪ)
- “Colleges I am applying to” የሚለውን አገናኝ ጠቅ በማድረግ “Common App Account Matching” የሚለውን ክፍል ሙላ(ይ)
- ተማሪዎች "Common App" አካውንት ለመክፈት የተጠቀሙበትን የኢሜል አድራሻ ማስገባት አለባቸው
- አካውንቶቹ በትክክል እንዲዛመዱ፣ የተማሪዎቹ የልደት ቀን፣ ስም፣ እና የኢሜይል አድራሻ በሁለቱም አካውንቶች ላይ አንድ አይነት መሆን አለባቸው - **ምንም የቅጽል ስም አያስፈልግም/NO NICKNAMES**

ደረጃ 4

## ለኮሌጅ የሚቀርብበትን ዘዴ እና ለማመልከት የምትፈል(ጊያ)ጋቸውን ኮሌጆች መወሰን አለብህ(ሽ)

- ተማሪዎች የሚያመለክቱትን ማንኛውንም ትምህርት ቤት “Colleges I am Applying to” ዝርዝር ውስጥ ማስገባት አለባቸው።
- ለእያንዳንዱ ትምህርት ቤት እንዴት እንደሚያመለክቱ መለየት ያስፈልጋል (Common Application, Coalition Application, or directly to the school’s site [eDocs]) ብዙ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች ለማመልከት የሚጠቀሙባቸው በርካታ ዘዴዎች ይኖራቸዋል። በትክክል ካልተገለጸ በስተቀር ፋይሎችን መላክ አይቻልም።
- በየትኛው ቀነገደብ እንደምታመለክት(ቺ) መለየት ያስፈልጋል፡-(Early Decision, Early Action, Regular Decision, Rolling)
- ትምህርት ቤቱ የጽሑፍ ማመልከቻ የሚፈልግ ከሆነ የበለጠ መረጃ ለማግኘት ወደ ደረጃ 5 ቀጥል(ይ)።

ደረጃ 5

## በፖስታ ቤት በኩል የሚቀርብ ማመልከቻ

- ለት/ቤት በፖስታ ቤት በኩል በሚላክ ማመልከቻ የምታመለክት(ቺ) ከሆነ፣ ስም የተጻፈበት (የመመለሻ አድራሻ ያልተጻፈበት) 3 አንደኛ ደረጃ ቴምብር ወይም ተመሳሳይ ዋጋ ያለው በፖስታው ላይ የተለጠፈ 9x12 ኤንቨሎፕ፣ ለኮሌጅ ምዝገባ ቢሮ ወይም ለስኮላርሺፕ ፕሮግራም አቅርብ(ቢ)።

ደረጃ 6

## ትራንስክሪፕት መጠየቅ እና ማመልከቻ ማቅረብ

- ትራንስክሪፕቱ በፖስታ ወይም በኦንላይን የሚቀርብ ከሆነ በኦንላይን የትራንስክሪፕት መጠየቂያ ቅጽ መሙላት ያስፈልጋል። ካውንስለርህ(ሽ) አስፈላጊ ሰነዶችን መላክ እንዳለበት ማወቅ የሚችለው በዚህ መንገድ ብቻ ነው። ቅጹ እዚህ ተያይዟል፥ AEHS ካውንስሊንግ ገጽ ላይ በቀኝ በኩል "AEHS Class of 2026 የኮሌጅ ማመልከቻ ማቅረቢያ ቅጽ" ይባላል።
- የአንተ(ቺ)ን ድርሻ (ማመልከቻ፣ ድርሰት፣ እና ክፍያ) በቀጥታ ለኮሌጅ/ለዩኒቨርሲቲ - በኦንላይን ወይም በፖስታ እንዲደርስ አድርግ(ጊ)።

7ኛ

## የአስተማሪ አስተያየት መስጫ ጥያቄ

- Family Connection/Naviance ወይም የፖስታ መልክት ይጠቀም/ትጠቀም እንደሆነ ለማወቅ አስተማሪህ(ሽ)ን አነጋግር(ሪ)። በፖስታ ከሆነ ለእያንዳንዱ ኮሌጅ አንድ ቴምብር ያለበት መደበኛ ፖስታ/ኤንቬሎፕ አቅርብ(ቢ)። የማመልከቻ ቀነ ገደብ መኖሩን ለአስተማሪህ(ሽ) መግለጽ ያስፈልጋል (Naviance ከሆነም ተመሳሳይ ቀን ይሆናል)። መጠሪያ ስም እና የአያት ስምህ(ሽ)ን በፖስታው በስተግራ በላይኛው ጠርዝ ላይ ፃፍ(ፊ)። ፖስታው ላይ የመመለሻ አድራሻ አትጻፍ(ፊ)በት።
- የአስተማሪ አስተያየት መላክ ያለበት eDocs ላይ ከሆነ፣ ጥያቄው "Family Connections/Naviance" አካውንት ላይ መቅረብ አለበት።

8ኛ

## SAT እና/ወይም ACT ውጤት በቀጥታ ለኮሌጅ እንዲላክ መጠየቅ አለብህ(ሽ)።

- በኦንላይን SAT ውጤት ለመጠየቅ @http://sat.collegeboard.org/scores እና ACT ውጤት ለመጠየቅ http://actstudent.org/scores/send መሞላት አለበት።
- የአልበርት አንስታይን ት/ቤት የተማሪዎችን የፈተና ውጤት ለማግኘት አይችልም። ራስህ(ሽ) ማቅረብ ይኖርብሃ(ሻ)ል።